

# ጸሎታችንን ሰይጣን እንዴት እንደሚከለክል

## ውጊያ በሰማያዊ ግዛት

በጆን ሙሊንዴ፥ ኦብስቴግ (ኦስትሪያ) ኖቬምበር 2000 (እ.ኤ.አ.)

(*by John Mulinde, Obsteig (Austria) Nov. 2000* www.DivineRevelations.info/COMBAT)

ዛሬ የአንድን የዳነን ሰው ምስክርነት ላጋራችሁ እፈልጋለሁ፥ ሰይጣንን ያገለግል የነበረ ሰው። ይህ ሰው ምስክርነቱን ሲሰጥ፥ በጣም ፈትኖኝ ነበር፥ ለማመን አልፈለግሁም። በጌታ ፊት ለአስር ቀናት መጾም ነበረብኝ፥ ጌታን እየጠየቅሁ፤ "ጌታ ሆይ፥ ይህ እውነት ነውን?" እንደግዲህ በዛ ሠዓት ነው ጌታ በምንጸልይ ጊዜ በመንፈሳዊ ግዛቶች የሚሆነውን ሊያስተምረኝ የጀመረው።

ይህ ሰው የተወለደው ቤተሰቦቹ ራሳቸውን ለሰይጣን ካስገዙ በኋላ ነው። ገና በማህጸን ሳለ፥ ሰይጣንን ያገለግል ዘንድ ብዙ ስርዓቶችን ፈጽመዋል። ገና በአራት ዓመት እድሜው፥ መንፈሳዊ ኃይሉን መለማመድ ጀመረ። እናም ቤተሰቦቹ ይፈሩት ጀመር። ስድስት ዓመት ሲሞላው አባቱ ሄዶ እንዲያሰለጥኑት ለ(ሴት) መተተኞች (ጠንቋዮች) አሳልፎ ሰጠው። እናም በአስር ዓመቱ፥ በሰይጣን ግዛት ውስጥ ታላላቅ ነገሮችን ያደርግ ነበር። በተራ መተተኞችም ይፈራ ነበር።



ገና ወጣት ልጅ ነበር፥ ነገር ግን በሚሠራው ሥራ የሚፈራ ነበር። አድጎም በሃያዎቹ እድሜ ክልል የሚገኝ ወጣት በሆነ ጊዜ፥ የብዙ ሰዎች ደም በእጁ ነበር። እንደፈቀደ ይገል ነበር። በ(ክፉ)መንፈሳዊ ልምምድ ከሰውነቱ ወጥቶ የመሄድ ችሎታ ነበረው። (ትራንሲደንታል ሜዲቴሽን፣ transcendental meditation) እናም በአየር ላይ መንሳፈፍ ይችል ነበር። አንዳንድ ጊዜ ሰውነቱ ከምድር ይነሳና በአየር ላይ ይቆም ነበር። አንዳንዴ ደግሞ፥ ይመሰጥና ከሰውነቱ ውስጥ ይወጣል፤ ሰውነቱ እዚያው ይቀራል፤ እርሱም በዓለም ሁሉ ይሄዳል፤ ይህም የህዋ ላይ ጉዞ (አስትሮ-ትራቭሊንግ፣ astro-travelling) ይባላል። እናም ሰይጣን ልጁን ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን ለማጥፋት ይጠቀምበት ነበር፥ ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን ለመከፋፈልና ብዙ መጋቢዎችን (ፓስተሮችን) ለማጥፋት።

አንድ ቀን፥ በጸሎት የተሞላን ቤተክርስቲያን ለማጥፋት ተመደበ፤ በዚህ ቤተክርስቲያን ውስጥ ብዙ መከፋፈልና አለመግባባቶች ነበሩ። እናም እዚህ ቤተክርስቲያን ውስጥ መሥራት ጀመረ። ነገር ግን በዚያ ሠዓት፥ መጋቢው (ፓስተሩ) ምእመናኑ ሁሉ እንዲጾሙ ጥሪ አቀረበ። ምእመናኑ መጾም ሲጀምሩ፥ ብዙ ንስሐና መግባባቶች ሆኑ። እናም ሰዎቹ ወደ አንድነት መጡ፥ እናም በመካከላቸው ጌታ እንዲሠራ መጸለይ ጀመሩ። ከዛም በህይወታቸው እንዲገባ ይቅርም እንዲላቸው ወደ እግዚአብሔር መጸለይና መማለድ ጀመሩ። እናም ጊዜው እያለፈ ሲሄድ፥ ሰውየው በቤተክርስቲያኗ ላይ እየደጋገመ ክፉ መናፍስትን ይዞ መምጣቱን ቀጠለ። ነገር ግን ቤተክርስቲያኗን በሚያጠቃት በጨለማ ኃይላት ላይ ውጊያቸውን እንዲቀጥሉ የሚነግራቸው የትንቢት ቃል ወደ ክርስቲያኖቹ መጣ።

ከእለታት በአንዱ ቀን ይህ ሰው ሰውነቱን በክፍሉ ውስጥ ትቶ ወደ ህዋ ጉዞው ሄደ። በዚህ ቤተክርስቲያን ላይ ታላቅ የአጋንንት ሠራዊትን እየመራ (እንደ አዛዥ፣ ፊታውራሪ) ነበር። አሁን ይህ የእርሱ ምስክርነት ነው። መንፈሱ በአየር ላይ በቤተክርስቲያኗ ላይ እየሄደ ሊያጠቃት ይሞክራል፥ ነገር ግን በቤተክርስቲያኗ ላይ የብርሃን ሽፋን ነበር። እናም በድንገት የሚዋጋቸው የመላእክት ሠራዊት መጣ፥ እናም በአየር ላይ ጦርነት ሆነ፥ እናም ሁሉም አጋንንት ሸሹ፥ እርሱ ግን በመላእክቱ ተማረከ።

አዎን፥ በመላእክቱ ተማረከ! እራሱን ወደ ስድስት በሚሆኑ መላእክት ተይዞ አየ። እናም በጣሪያው ውስጥ አድርገው እስከ ቤተክርስቲያኑ መድረክ ድረስ አመጡት። እንግዲህ ይኸውና፥ ሰዎቹም እየጸለዩ ነው። በተመስጦ እየጸለዩ በመንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ እያሰሩ፣ እየሰባበሩ፣ እያስወጡ። መጋቢው ጸሎቱንና ውጊያውን እየመራ በመድረኩ ላይ ነበር። የእግዚአብሔር መንፈስ ለመጋቢው ተናገረው፣ "*ወጥመዱ ተሰብሯል፥ ተጎጂውም በፊትህ ነው። ነፃ ይወጣ ዘንድ እርዳው።*" መጋቢው አይኑን በገለጠ ጊዜ ይህንን ወጣት በፊቱ ወድቆ ያየዋል። ሰውነቱ ከእርሱ ጋር ነበር፥ ሥጋዊ አካሉ ውስጥ ነበር። ወጣቱም፥ ሰውነቱ እንዴት እንደተጋጠመ እንደማያውቅ ተናገረ፤ እቤቱ ትቶት ነበር። ይኸው አሁን በሰውነቱ ውስጥ ነው፥ መላእክቱ በጣሪያው ውስጥ ይዘውት ሲያልፉ እንኟ እንዴት እንደገባ አያውቅም።



አሁን፥ እነዚህ ነገሮች ለማመን አስቸጋሪዎች ናቸው፥ ነገር ግን መጋቢው ምእመናኑን ዝም አስባላቸውና ጌታ የነገረውን ነገራቸው፥ እናም ወጣቱን ሰው ጠየቀው "*ማነህ አንተ?*" ጋኔሎቹ ከውስጡ ሲወጡ ወጣቱ እየተንቀጠቀጠ ነበር። ከዛም ነፃ ይወጣ ዘንድ ጸለዩለትና ህይወቱን ማጋራት ጀመረ። ይህ ወጣት አሁን ወደ ጌታ መጥቷል፥ ሰባኪም ሆኖ ወንጌልን ይሰብካል። ጌታ ሌሎችን ነፃ ለማውጣት በታላቁ እየተጠቀመበት ይገኛል።

በአንድ ምሽት፥ እኔ (ጆን ሙሉንዴ) ወደ እራት ግብዣ ሄድኩኝ። የሄድኩበት ዋናው ምክንያት የሆነ ሰው ስለወጣቱ ሰው ስለነገረኝ ነው፥ እናም ላየው ጓጉቼ ነበር፥ እናም ታሪኩ እውነተኛ መሆኑን ለማረጋገጥ። ስለዚህ በእራቱ ላይ ተገኘሁ፥ ማታ ላይ፥ ሰውየው የራሱን ምስክርነት እንዲሰጥ እድል ተሰጠው። ስለብዙ ነገሮች ተናገረ። አንዳንዴ በሠራው ሥራ ያለቅሳል። እንደጨረሰ ማሳሰቢያ ሰጠ።



በክፍሉ ብዙ መጋቢዎች ነበሩ። እንዲህ አለ "*እናንተ መጋቢዎች፥ ይህን አሳስባችኋለሁ፥ እባካችሁ ለሕዝቡ እንዴት መጸለይ እንዳለባቸው ንገሩ።*" የማይጸልዩ ሰዎች፥ በማንኛውም ነገር ሊወሰዱ ይችላሉ፥ በማንኛውም ነገር በሰይጣን ይወሰዳሉ፥ ጠላት ህይወታቸውንና ጸሎታቸውን ለራሱ የሚጠቀምበት መንገድ አለው። ጠላት፥ እንዴት መጸለይ እንዳለባቸው የማያውቁትን፥ ጸሎታቸውን እንኳ ለራሱ እንዴት መጠቀም እንዳለበት ያውቃል። "*ለሕዝቡ እግዚአብሔር የሚሰጣቸውን የጦር እቃ እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው አስተምሯቸው።*"

ከዛም በአየር ላይ ክንውኖችን እንዴት እንደሚመራ አካፈለ። ከሌሎች የሰይጣን መልእክተኞችና ከሰይጣን መናፍስት ጋር በመሆን ወደ አየር ይሄዳል። እንደተራ ዓይነት ነው፥ በተራችሁ ትሄዱና ትሠራላችሁ። ስለዚህ ወደ ሰማያት ሄዶ ውጊያ የሚያከናውንበት መደበኛ ሠዓት አለው። እናም እንዲህ አለ በሰማያት፥ በመንፈሳዊው ዓለም፥ ምድሪቱ በጨለማ ብርድልብስ ከተሸፈነች፥ ያ ብርድልብስ በጣም ጠንካራ ነው፥ ልክ እንደ አለት። እናም መላዋን አካባቢ ይሸፍናል። እናም መናፍስቶቹ ከዚህ ብርድልብስ በላይም ሆነ በታች መሄድ ይችላሉ። እናም ከዚህ ስፍራ በምድር ላይ ያሉ ነገሮች ላይ ተጽእኖ ያደርጋሉ።

ክፉ መናፍስቱና የሰው መልእክተኞቻቸው ተራቸውን ሲለቁ፥ ቃል ኪዳን ወደ ተገባቡበት ቦታ ወደ ምድር፥ በውኃዎችም ጭምር አልያም በመሬት በቃል ኪዳን ቦታቸው መንፈሳቸውን ለማደስ ይሄዳሉ። እና እንዴት ነው መንፈሳቸውን የሚያድሱት? ሰዎች በእነዚህ መሰዊያዎች በሚሰጧቸው መስዋዕት። መስዋዕቶቹ ግልጽ የሆኑ መተቶች፣ አልያም ደም በማፍሰስ፥ ማንኛውንም ዓይነት፥ ውርጃ፣ ጦርነት እናም የሰው ወይም የእንስሳት መስዋዕት ሊሆን ይችላል። እንዲሁም መስዋዕቶቹ በአመንዝራነት፣ ልቅ በሆነ ጾታዊ ግንኙነቶች፥ እንዲሁም ወጣ ያሉ ጾታዊ ግንኙነቶችም ሊሆኑ ይችላሉ። እናም ይህ ተግባር የእነዚህን ኃይላት ጥንካሬ ያግዛል። እናም ሌሎች ብዙ የሚቀርቡ የመስዋዕት ዓይነቶች ናቸው።

እርሱ እንዳለው የሰይጣን መልእክተኞቹ በሰማያዊ ግዛቶች ሲሆኑና፥ ክርስቲያኖች በምድር መጸለይ ሲጀምሩ፥ የክርስቲያኖቹ ጸሎት በሦስት መልኩ ይገለጽላቸዋል። ሁሉም ጸሎትች ወደ ሰማይ እንደሚያርግ እንደ ጢስ ሆነው ይታያሉ።



አንዳንድ ጸሎቶች እንደ ጢስ ሆነው ይመጣሉ፥ ከዛም በመንገድ መበታተን ይጀምሩና ይጠፋሉ። እነዚህ ጸሎቶች በህይወታቸው ኃጢአት ያለባቸውና ይህንንም ማስወገድ የማይፈልጉ ሰዎች ጸሎት ነው። ጸሎቶቻቸው በጣም ደካማ ናቸው፥በንፋስ ይወሰዱና ይጠፋሉ።



ሌላኛውም ጸሎት ልክ እንደ ጢስ ነው እናም እስከ አለቱ ድረስ ይወጣል፥ ነገር ግን አለቱን ሰብሮ ማለፍ አይችልም። እነዚህ፥ ብዙውን ጊዜ ራሳቸውን ሊያነጹ የሚፈልጉ ሰዎች ናቸው፥ ነገር ግን እየጸለዩ ሳለ በሚያደርጉት ነገር ላይ እምነት ያንሳቸዋል። ብዙውን ጊዜ አንድ ሰው በሚጸልይበት ጊዜ የሚያስፈልጉትን ወሳኝ ነገሮች ቸል ይሏቸዋል።



ሦስተኛው ዓይነት ጸሎት ልክ በእሳት እንደተሞላ ጢስ ዓይነት ነው፥ ወደ ላይ በሚሄድበት ጊዜ ወደ አለቶቹ ሲደርስ በጣም የሚያቃጥል ነው፥አለቱም እንደ ሰም መቅለጥ ይጀምራል። አለቱን ይበሳና አልፎ ይሄዳል።

ብዙ ጊዜ ሰዎች መጸለይ ሲጀምሩ፥ጸሎታቸው የመጀመሪያውን ዓይነት ይመስላል፥ ነገር ግን ጸሎታቸውን ሲቀጥሉ እንደ ሁለተኛው ዓይነት ይሆናል። ከዛም ጸሎታቸውን ሲቀጥሉ በድንገት እንደ እሳት ይቀጣጠላል። እናም ጸሎቶቻቸው በጣም ኃይለኛ ይሆኑና አለቱን ሰንጥቀው ያልፋሉ።

ብዙ ጊዜ ክፉ ተላላኪዎች ጸሎቶቹ እየተቀየሩና እሳት ወደ መሆን በጣም መቃረባቸውን ያስተውላሉ፥ ከዛም እነዚህ መልእክተኞች በምድር ካሉ ሌሎች መናፍስት ጋር ግንኙነት ይፈጥሩና ይነግሯቸዋል፤ “*ያን ሰው ከጸሎቱ አሰናክሉት። ጸሎቱን አስቁሙት። ኀትታችሁ አውጡት።*”

ብዙ ጊዜ ክርስቲያኖች ለዚህ መሰናክል ይጋለጣሉ። እየታገሉ ነው፥ ንስሐ እየገቡ ነው፥ ቃሉ መንፈሳቸውን እንዲያነቃቃው እየፈቀዱ ነው፥ እምነታቸው ተገንብቷል። ጸሎታቸው በጣም ያተኮረ እየሆነ ነው። ከዛም ሰይጣን ጸሎታቸው ኃይል እያገኘ እንደሆነ ያያል ከዛም ማሰናከሉ ይጀምራል። ስልኮች ይጮሀሉ። አንዳንድ ጊዜ እኛ፥ በጣም በጣም ጥልቅ በሆነ ጸሎት ውስጥ ሆነን፥ ስልክ ይጮሀል፥ ከዛ ሄዳችሁ ስልኩን አንስታችሁ መጥታችሁ እንደገና ለመጸለይ ተሰባላችሁ። ተመልሳችሁ ስትመጡ፥ ወደ መጀመሪያው ደረጃ ትመለሳላችሁ። እናም ሰይጣን የሚፈልገው ይህንን ነው።



ሌሎችም ዓይነት ማሰናከያዎች በመንገዳችሁ ይመጣሉ፥ ሰውነታችሁን የሆነ ቦታ መንካትና ህመም እንዲሰማችሁ ማድረግ እንኳ ቢሆን። አልያም እንዲርባችሁና ወደ ጓዳ ሄዳችሁ የሆነ ነገር ሠርታችሁ መብላት እንድትፈልጉ ማድረግ እንኳ ቢሆን። ከዛ ቦታ እስካስወጡአችሁ ድረስ፥ አሸንፈዋችኋል። እናም ለመጋቢዎቹ እንዲህ ይላቸዋል “*ለሰዎች አስተምሩ። የሆነ ሠዓት መድቡ። ያለ እቅድ ለሚደረግ ጸሎት አይደለም። ያንን ቀኑን ሙሉ ሊያደርጉት ይችላሉ። በቀን አንዴ፥በሙሉ ልባቸው፥በእግዚአብሔር ላይ በሙሉ ልባቸው የሚያተኩሩበት ሠዓት ያስፈልጋቸዋል፥ ምንም የሚረብሻቸው፣ የሚያሰናክላቸው ሳይኖር።*”

እናም ሰዎች በዚህ ዓይነት ጸሎት ቢጸኑና ራሳቸውን በመንፈስ ቢያነሳሱ እናም ሳይታክቱ ቢቀጥሉ፥ በመንፈስ የሆነ ነገር ይፈጠራል። እሳቱ ያን አለት ይነካውና ያቀልጠዋል። እናም፥ መቅለጡ ሲጀምር በጣም ያቃጥላል፥ ማንም የሰይጣን መንፈስ ሊቋቋመው አይችልም። ማንም የሰው መንፈስ ሊቋቋመው አይችልም። ሁሉም ይሸሻሉ። ሁሉም ይጠፋሉ።



ይሄኔ በመንፈሳዊው ግዛት ክፍተት (ቀዳዳ) ይፈጠራል። እናም ይህ እንደሆነ፥ በጸሎት ጊዜ የሚያስቸግረን ሁሉ ይጠፋል። በምድር ላይ የሚጸልይ ሰው፥ በድንገት ጸሎቱ ወጥ የሆነ ዓይነት ስሜት ይሰማዋል፥ የሚያስደስት፣ ኃይለኛና ጽኑ። እናም የተረዳሁት ነገር፥ በዚህ ቅጽበት ሠዓቱንም ሌሎችም ነገሮችን አናስተውልም። ሁሉም ነገር ተደበላልቆብናል ለማለት ግን አይደለም። እግዚአብሔር ሠዓቶቻችንን ይቆጣጠራል። ነገር ግን ልክ ሁሉንም ነገር ትታችሁ ከእግዚአብሔር ጋር እንደመጣበቅ ነው። እናም ይህ ሰው እንዳለው፥ ጸሎቶቹ ሰንጥቀው ሲያልፉ፥ ከዚያ ቅጽበት ጀምሮ ምንም የሚቋቋመው ነገር ፈጽሞ አይኖርም፥ እናም የሚጸልየው ሰው እስከፈለገው ድረስ መቀጠል ይችላል። ሊያስቆመው የሚችል ምንም ዓይነት ተቃዋሚ የለም።

እናም እንዲህ አለ፥ ጸሎቱን ከጨረሰ በኋላ ክፍተቱ እንዳለ ይቀራል፥ እናም ሰውየው እንዳለው፥ ከጸሎት ቦታቸው ተነስተው ሲወጡ፥ ይህ ክፍት ቀዳዳ አብሯቸው ይጓዛል። ከዚህ በኋላ የሚሠሩት፣ የሚንቀሳቀሱት ከብርድልብሱ ስር ሆነው አየደለም። የሚሠሩት ከተከፈተች ሰማይ ስር ሆነው ነው። እናም እንዳለው፥ በዚህ ደረጃ ሰይጣን በእነርሱ ላይ የፈለገውን ነገር ማድረግ አይችልም። እናም ጌታ በእነርሱ ህይወት ውስጥ አርፎ እንደ ማእዘን ድንጋይ ሆኖ ይኖራል። የተጠበቁ ናቸው፥ እናም በዚያ የማእዘን ድንጋይ ውስጥ ታላቅ ኃይል አለ በመሆኑም በተንቀሳቀሱ ጊዜ ሁሉ፥ ይህ ኃይል ሌሎችን ሰዎች ይነካል። ጠላት በሌሎች ሰዎች ህይወት ውስጥ የሠራውን ይለያል (ያውቃል።) እናም እነርሱ ከሰዎች ጋር ሲያወሩና እነዚያም ሰዎች አብረዋቸው ሲቆሙ፥ በማእዘኑ አለት ውስጥ ይሆናሉ። እናም በማእዘኑ አለት ውስጥ እስከቆዩ ድረስ፥ የጠላት እስር ሁሉ ይደክማል።



ስለዚህም እነዚህ በመንፈስ ሰብረው የወጡ ሰዎች ለኃጢአተኞች ስለክርስቶስ ሲያካፍሏቸው፥ (ኃጢአተኞች) የመቋቋም ኃይላቸው ደካማ ነው። እነርሱን ወደ ውስጥ ለማምጣት ይቀላቸዋል። ስለታመሙ ሰዎች ሲጸልዩ ወይም ስለነገሮች ሲጸልዩ፥ በዚያ ያለው የእግዚአብሔር ኃይል ሁሉን ለውጥ ያደርጋል። እናም ይህ ሰው እንዳለው ሰይጣን እነዚህን ሰዎች ይጠላቸዋል። እናም እንደተባለው እንደዚህ ዓይነት ጸሎቶች ተዘውትረው የሚጸለይባቸው ቦታዎች ካሉ፥ የእግዚአብሔር ኃይል ወደዚያ ቦታ ይመጣል እናም ፈጽሞ አይሄድም። በመሆኑም እግዚአብሔርን የማያውቁ ሰዎች እንኳን ወደዚያ ቦታ ቢመጡ፥ በድንገት እስራታቸው ይቀላል (ይደክማል።)

እናም አንድ ሰው በፍቅርና በትእግስት ሊሰብካቸው ቢገደው (ቢፈቅድ)፥ በቀላሉ ሊሳቡ ይችላሉ፥ በኃይልና በግድ አይደለም፥ ነገር ግን በዚያ ባለው በእግዚአብሔር መንፈስ። እናም እንዲህ አለ፥ ነገር ግን ማንም ስለነዚህ ሰዎች ግድ ካላለው፥ እግዚአብሔር ወዳለበት ይመጣሉ፥ ይወቀሳሉ፥ ለመቆየት አልያም ላለመቆየት ያመነታሉ፥ ነገር ግን ወደ ውስጥ ካልተሳቡ፥ ከዚህ ቦታ ወጥተው ሲሄዱ፥ እስራታቸው ይጠነክራል። እናም ሰይጣን ወደዚህ ቦታ ተመልሰው እንዳይመጡ የተቻለውን ሁሉ ጥረት ያደርጋል።

ሁላችንም ተቀምጠን ይህን ሰው ስንመለከተው ማሰብ ትችላላችሁ። ሲያደርጋቸውና ሲያያቸው የነበሩትን ነገሮች ነው እየነገረን ያለው። ከዛም በጸሎታቸው ሰብረው በወጡ ሰዎች ላይ ደግሞ የሚያደርጉትን ነገረን። እንዳለው እንደነዚህ ዓይነት ሰዎችን ኢላማ ያደርጓቸዋል፣ እንደነዚህ ዓይነቶቹን ሰዎች ያጠኗቸዋል። ስለነዚህ ሰዎች ለማወቅ የሚችሉትን ሁሉ ይቆፍራሉ። ድካማቸውን ያውቁ ዘንድ፥ እናም የሆነ ሰው በጸሎቱ ሲያሸንፋቸውና ሰብሮ ሲወጣ፥ ከሌሎች መናፍስት ጋር ይገናኙና እንዲህ ይባባላሉ፥ *"በእነዚህ፣ በእነዚህና በእነዚህ ነገሮች ይህን ሰው አጥቃው። ደካማ ጎኖቹ እነዚህ ናቸው።"* ስለዚህ ይህ ሰው ከጸሎት ክፍሉ ሲወጣ፥ የጸሎት መንፈስ በላዩ ነው፥ የእግዚአብሔርም ኃይል በእርሱ ነው፥ መንፈሱ ከፍተኛ ነው፥ የጌታ ሰላም ብርታቱ ነው። በሚንቀሳቀስበት ጊዜ ጠላት ትኩረቱን በጌታ ላይ እንዳያደርግ ሊያዘናጉት የሚችሉትን እነዚያን ነገሮች ለማምጣት ይሞክራል።

ደካማነቱ በንዴት በኩል ከሆነ፥ እንግዲያው ጠላት ሰዎች በጣም የሚያናድደውን ነገር እንዲያደርጉ ያደርጋል። እናም ለመንፈስ ቅዱስ ቶሎ ምላሽ የማይሰጥ ከሆነ፥ እናም እራሱን ለንዴት አሳልፎ ከሰጠ፥ ዓይኑን ከጌታ ላይ ያነሳል። ይናደዳል፥ ቁጡነት ይሰማዋል፥ እናም ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ፥ ያንን ትቶ በእግዚአብሔር ሰላም ለመጓዝ ይሞክራል፥ ነገር ግን ከዛ በኋላ ሊሰማው አይችልም። እንደገና ጥሩ ስሜት

እንዲሰማው ለማድረግ ይሞክራል፤ ነገር ግን እንደገና ጥሩ ስሜት አይሰማውም። ለምን? እርሱ ለፈተናው እጅ ሲሰጥ፥ እነርሱ የላይኛውን በር ለመዝጋት ብዙ ጥረት አድርገዋል። እናም አንዴ አለቱን ከመለሱት፥ ያ ኃይል ይቋረጣል። ሰውየው የእግዚአብሔር ልጅነቱን አያጣም። ነገር ግን በህይወቱ ውስጥ የነበረው ተጨማሪ ጸጋ፥ እርሱ ምንም ሳያደርግ ነገሮችን ማድረግ የሚችለው ኃይል ይቋረጣል። ድክመቱ የሚገኝበትን ነው የሚፈልጉት።

የሚፈተነው በጾታዊ ነገር ከሆነ፥ ጠላት ስሜቱን፣ ፍላጎቱን ወደ እዛ ፈተና በድንገት የሚወስዱ ሰዎችን፣ ሁኔታዎችን፣ ወይም ሌሎች ነገሮችን ያዘጋጃል። እናም ይህ ሰው ለዚህ ፈተና ከተሸነፈና አእምሮውን ለእነዚህ ሀሳቦች ከከፈተና ካስተናገዳቸው፥ ከሁሉ በኋላ እንደገና ተመልሶ በጸጋው ለመጓዝ ሲሞክር፥ ከእንግዲህ ከእርሱ ጋር እንዳሌለ ይረዳል። ምናልባት እንዲህ ልትሉ ትችላላችሁ "*ይህ ፍትሐዊ አይደለም።*" ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን አስታውሱ "*የመዳንን ራስ ቁር አጥልቁ። የጽድቅንም ጥሩር ልበሱ።*" ([ኤፌሶን 6፥10-18](#)) እኛ በተለምዶ የውጊያው ጦር መሳሪያዎች የሚያርፉባቸውን ቦታዎች አናውቃቸውም። ነገር ግን ኢየሱስ በጌታ ጸሎት መጨረሻ ላይ የነገረንን አስታውሱ "*ወደ ፈተና አታግባን ከክፉ ሁሉ አድነን እንጂ።*" ([ሉቃስ 11፥2-4](#))

ሁል ጊዜም በጸሎት ሰብራችሁ በወጣችሁ ጊዜ፥ በመጨረሻ፥ ደካማ ሰው መሆናችሁን አስታውሱ። ገና ፍጹም አለመሆናችሁን አስታውሱ። ጌታን "*ጌታ ሆይ፥ በዚህ የጸሎት ሠዓት ደስተኛ ነበርኩ፥ ነገር ግን ወደ ዓለም ስወጣ፥ ወደ ፈተና አታግባኝ። ወደ ሰይጣን ወጥመድ እንድገባ አትፍቀድ። ጠላት በውጭ ወጥመድን እንዳስቀመጠ አውቃለሁና። እኔ ምን መስሎ እንደሚመጣ አላውቅም። እናም እኔ እስካሁን በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ደካማ እንደሆንኩ አውቃለሁ። በትክክለኛው ቦታ ብቀመጥ ያንን መቋቋም እችላለሁ። ጠብቀኝ ጌታ ሆይ። ወጥመዱ ወዳለበት ቦታ ስታጠፍ ብታየኝ፥ ወደ ሌላኛው አቅጣጫ እንድታጠፍ አድርገኝ። ጣልቃ ግባ፥ኦ ጌታ ሆይ። በራሴ ብርታትና እውቀት እንድጓዝ አትፍቀድ። ከክፉ ሁሉ አድነኝ።" ([2ኛ ጢሞቲዎስ 3፥7](#))*

እግዚአብሔር ያን ማድረግ ይችላል። ይቻለዋል። ለዚህ ነው አንዳንድ ጊዜ ነገሮች የሚከናወኑት፥ ማለት የሚጠበቅባችሁ፥ "ኢየሱስ ሆይ፥ አመሰግንሀለሁ።" ብቻ ነው። ለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ በተሰሎንቄ መልእክቱ እንዲህ ብሎ የጻፈው፥ (*[1ኛ ተሰሎንቄ 5፥17](#)*) "*እግዚአብሔርን በነገር ሁሉ አመስግኑት ይህ በክርስቶስ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነውና።*" አንዳንድ ነገሮች ጥሩ አይደሉም። የሚያሳምሙ ናቸው፥ እናም እግዚአብሔር ይህን ለምን ፈቀደ ብለን ልናስብ እንችላለን። ነገር ግን ከምን እያዳነን እንደሆነ ብናውቅ፥ እናመሰግነው ነበር። ጌታን ማመን ስንማር፥ በሁሉ ነገር ዝም ብለን እናመሰግነዋለን።

የተወደዳችሁ ሆይ፥ በጥልቅት መሄድ ይኑርብኝ አይኑርብኝ አላውቅም፥ ምክንያቱም ልጨርሰው የማልችለውን ነገር መጀመር አልፈልግም። አንድ እርምጃ ብቻ ወደ ፊት ልሂድ። እናም ይህ ሰው እንዳለው ጸሎት እንደዛ ሰብሮ ሲወጣ፥ መልስ ሁል ጊዜ ይመጣል። እርሱ እንዳለው ጸሎት እንደዛ ሰብሮ ወጥቶ ያልተመለሰበት አጋጣሚ አያስታውስም። እንዳለውም መልስ ሁል ጊዜ ይመጣል፥ ነገር ግን ብዙ ጊዜ፥ ወደ ጠየቀው ሰው አይደርስም። ለምን? በሰማይ ባለ ጦርነት። እርሱ እንዳለው ክፍቱን ሰማይ ለማቋረጥና አለቱን ለመመለስ እስከተሳካላቸው ድረስ፥ ይህን ሰው ይከታተሉታል፥ የሚጠባበቁበትም ምክንያት መልስ በእርግጠኝነት እንደሚመጣ ስለሚያውቁ ነው።

እናም ይህ ሰው እምነቴን የተፈታተነ አንድ ነገር ተናገረ። ከዚህ ቀጥሎ በተናገረው ነገር ምክንያት ነው ወደ አስር ቀን ጾም የገባሁት፥ ጌታ ሆይ፥ ይህ እውነት ነውን? ልታረጋግጥልኝ ትችላለህ? ሰውየው ሁሉም ክርስቲያኖች የሚያገለግሏቸው መላእክት እንዳላቸው ተናገረ። አሁን መጽሐፍ ቅዱስ መላእክት እኛን የሚያገለግሉ መናፍስት ናቸው እንደሚል እናውቃለን። ([ዕብራውያን 1፥14](#)) እንዲህም አለ ሰዎች በሚጸልዩበት ጊዜ፥ መልስ በመልአኩ እጅ ይመጣል። መልአኩ መልሱን ልክ በትንቢተ ዳንኤል እንደምናነበው ይዞ ይመጣል። ከዛም በጣም ከባድ የሆነ ነገር ተናገረ፤ የሚጸልየው ሰው መንፈሳዊ መሳሪያዎቹን ካወቀና ከለበሳቸው፥ መልሱም ሙሉ በሙሉ የጦር እቃ በታጠቀ ወታደር ይመጣል።

የሚጸልየው ሰው ስለመንፈሳዊ የጦር እቃ ግድ ከሌለው፥ መላእክቶቻቸውም ያለ ጦር እቃ ይመጣሉ። በአእምሮአቸው ውስጥ ምን ዓይነት ሀሳብ እንደማይመጣ የማይጨነቁ ክርስቲያኖች። በህሊናቸው ውስጥ ያለውን ውጊያ አይዋጉም። መላእክቶቻቸው ያለ ራስ ቁር ይመጣሉ። በምድር ቸል የምትሉት ማንኛውም መሳሪያ፥ መልአኩ እናንተን ሲያገለግል አይኖረውም። በሌላ አገላለጽ፥ መንፈሳዊ የጦር እቃችን ሥጋዊ ሰውነታችንን አይደለም የሚጠብቀው፤ መንፈሳዊ አገልጋዮቻችንን ነው የሚጠብቀው።



ይህ ሰው እንዳለው፥ መልአኩ እየመጣ እያለ፥ አተኩረው ያልተሸፈነ ቦታውን ይፈልጋሉ፥ ከዛ እነዛን ቦታዎች ያጠቃሉ። የራስ ቁር ከሌለው፥ ጭንቅላቱን ያጠቃሉ። የደረት መከላከያ (ጥሩር) ከሌለው ደረቱን ያጠቃሉ። ጫማ ከሌለው፥ በእሳት ላይ እንዲሄድ እሳትን ያዘጋጃሉ። አሁን ይህ ሰው ያለውን ነው እየደገምኩ ያለሁት። በእርግጥ "መላእክት እሳት ያቃጥላቸዋል?" ብለን ጠይቀነዋል። እና ምን እንዳለን ታውቃላችሁ? አስታውሱ ይህ መንፈሳዊ ውጊያ ነው። እነዚህ ከመናፍስት ጋር የሚታገሉ መናፍስት ናቸው። (ዳንኤል 10፥13) ውጊያው ጽኑ ነው፥ እናም የእግዚአብሔርን መልአክ ሲያሸንፉት፥ መጀመሪያ ኢላማ የሚያደርጉት በያዘው መልስ ላይ ነው፥ እናም ያንን ከእርሱ ይወስዳሉ፥ ያንን ነው ለጠንቋዮችና ለመተተኞች የሚሰጡት፥ እናም ሰዎች እንዲህ ይላሉ፥ "ይህን በመተት ነው ያገኘሁት።"

መጽሐፍ ቅዱስ በያዕቆብ መልእክት ላይ ምን እንደሚል አስታወሳችሁ? (ያዕቆብ 1፥17) በጎ ስጦታዎች ሁሉ ከእግዚአብሔር ናቸው። ታዲያ ሰይጣን ለወዳጆቹ የሚሰጠውን ከየት ነው የሚያመጣው? አንዳንድ መውለድ የማይችሉ ሰዎች ወደ መተተኛ ሀኪሞችና ሰይጣን አምላኪዎች ይሄዳሉ፥ እናም ያረግዛሉ! ያን ልጅ የሰጣቸው ማን ነው? ፈጣሪው ሰይጣን ነው? አይደለም! እስከመጨረሻው ከማይጸልዩት እየሰረቀ ነው። ኢየሱስም አለ "ተግታችሁ ጸልዩ።"(ማቴዎስ 26፥41) ከዛም እንዲህ አለ "ነገር ግን የሰው ልጅ በመጣ ጊዜ እምነትን ያገኝ ይሆን?" (ሉቃስ 18፥8) እዛው እየጠበቃችሁት ያገኛችሁ ይሆን? ወይስ ትታክቱና ጠላት የጸለያችሁበትን ይወስድባችኋል?

ከዛም ይህ ሰው መልሱን በመስረቅ ብቻ እንደማይረኩ ተናገረ። እንዲሁም መልአኩን የማገት ፍላጎትም አላቸው። እናም ሊዋጉት ይጀምራሉ። አንዳንድ ጊዜ ይሳካላቸውና ያግቱታል አለ። እናም እንዲህ አለ፥ ይህ በሚሆንበት ጊዜ ክርስቲያኑ በምድር ተጎጂ ነው። በዚያ ክርስቲያን የፈለጉትን ማድረግ ይችላሉ ምክንያቱም በመንፈስ ያለ ረዳት ቀርቷል።

እንዲህ አልኩት "መልአክ በሰይጣን ሠራዊት በእስር ሊቆይ ይችላል ማለትህ ነው?" ይህ ሰው እነዚህን ነገሮች በሚናገርበት ጊዜ ጥቅስ እንኳን አያውቅም ነበር። ብዙ ጥቅሶችን አያውቅም ነበር። ያጋጠመውን ብቻ እያካፈለ ነበር። ከዛም እንዲህ አለ፥ መልአኩን ለረዥም ጊዜ አይይዙትም ምክንያቱም በሌላ ቦታ ሌሎች ክርስቲያኖች ስለሚጸልዩ፥ ተጨማሪ ኃይል ይመጣል፥ እናም መልአኩ ነፃ ይወጣል። ሀላፊነት ያለበት ክርስቲያን ካልጸለየ ግን በእስር ይቆያል።" ከዛም ጠላት የራሱን መልአክ እንደ ብርሃን መልአክ አድርጎ ወደዚህ ሰው ይልካል፥ እናም ያኔ ነው መታለል የሚጀምረው። የውሸት ራዕዮችና የውሸት ትንቢቶች። የተሳሳተ አመራር፥ ማለቴ ምሬት፥ መንፈሳዊ መመሪት፥ ሁሉንም ዓይነት የተሳሳቱ ውሳኔዎችን መወሰን። እናም ብዙ ጊዜ ይህ ሰው ለሁሉም ዓይነት ጥቃቶችና እስሮች የተጋለጠ ነው።

እናም ጌታን ጠየቅሁት፥ ያ እራት የተሸበረ ነበር፥ በጣም የሚያሸብር። እንዲህ አልኩ "ጌታ ሆይ፥ ይህን ለማመን በጭራሽ እንኳ አልሞክርም።" ሁሉንም መተማመኔን፥ ደህንነቴን ሁሉ አስጠፋው። ጌታን ለመጠየቅ ስሄድ፥ ለአስር ቀናት ነበር፥ ጌታ ሁለት ነገሮችን አደረገ። የሰማኋቸውን ነገሮች ማረጋገጥ ብቻ አይደለም፥ ይህ ሰው በመንፈሳዊ ግዛት ምን እየተፈጠረ እንዳለ ሊነግረን ያልቻለውን ሁሉ እንዳይ አእምሮዬን ከፈተው። እናም ሁለተኛው፥ እነዚህ ነገሮች በሚሆኑበት ተሸናፊዎች ሳንሆን አሸናፊዎች እንድንሆን ማድረግ የሚገባንን እንዳይ ፈቀደልኝ። እናም ሦስት ነገሮችን ልናውቅ ይገባናል እናም ከእነዚህ ሦስት ነገሮች ጋር መዋሀድ።

አንደኛ፦ እንዴት በውጊያ መሳሪያዎቻችን መጠቀም እንዳለብን። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ጦር እቃ ይላቸዋል። የእኛ የጦር እቃ አይደለም፤ የእግዚአብሔር የጦር እቃ ነው። ስንጠቀምበት፥ እግዚአብሔር በእኛ ፈንታ እንዲዋጋ እንፈቅዳለን። ሁለተኛ፦ የሚረዱንን መናፍስት-የመላእክት-ለመንፈሳዊ ህይወታችን ያለውን ግንኙነት መረዳት። እናም እኛን በሚመለከት በመንፈስ ለሚሆነው ነገር በልቡናችን የሚፈጠረው ነገር እንደመሪ ቶሎ ማዳመጥ፣ ምላሽ መስጠት መቻል። ይህ ወደ ሦስተኛው ነገር ይወስደናል፤ እርሱም መንፈስ ቅዱስ ነው።

መንፈስ ቅዱስ እኛን የሚያገለግለንና ነገሮችን የሚያመጣልን አገልጋዮችን አድርገን መውሰድ የለብንም። የሚያስፈልገንን ለአብ ለመናገር በአብ እና በእኛ መካከል አይሯሯጥም። ያ የመላእክት ሥራ ነው። ነገር

ግን እርሱ ከእኛ ጎን ነው የሚቆመው። ምን እያደረገ? እየመራን፥ እያስተማረን፥ በትክክለኛው መንገድ እንድንጸልይ እየረዳን። እናም እነዚህ ነገሮች በመንፈሳዊ ግዛቶች ሲፈጠሩ፥ ይነግረናል፥ አንዳንዴም ሌሊት ከእንቅልፋችሁ ቀስቅሶ "***ጸልዩ***" ይላችኋል። እናንተም፥ "አይደለም! ሠዓቴ ገና አልደረሰም" ትላላችሁ። እናም እርሱ፥ "***አሁን ጸልዩ!***" ይላችኋል። ለምን? በመንፈስ ምን እየሆነ እንዳለ ያያል። አንዳንዴ እንዲህ ይላል "***ነገ-ጹሙ!***" እናንተም፥"ኦ፥አይደለም፥ሰኞ እጀምራለሁ!" ትላላችሁ።

ነገር ግን እርሱ በመንፈሳዊ ግዛቶች የሚሆነውን ይረዳል። ለመንፈስ ቅዱስ ቶሎ ምላሽ ለመስጠት መለማመድ ይኖርብናል። እርሱ ወደ ጽድቅ መንገድ ይመራናል። ወዳጆች እዚህ ጋር ልናቆም ይገባናል። ምን አልባት ነገ፥ በዚህ ውስጥ እንዴት መጸለይ እንደሚገባን፥ መንፈሳዊ ውጊያዎችን ማወቅና እንዴት ሰብረን እንደምናልፍ እንነጋገራለን። አንዴ ካገኘነው በኋላ ሰብረን መውጣታችንን እንዴት ነው አጽንተን ልንጠብቅ የምንችለው። እናም አንዴ እነዚህን ከተማርን፥ አስደሳች ይሆናል። ከዛም አንድ ነገር እንማራለን፤ ውጊያው የእኛ እንዳልሆነ፤ ውጊያው የጌታ ነው! ሃሌ ሉያ!



ዝም ብለን እንነሳ። አንድን ሰው ዓይኑን ተመልከቱት፥ እናም ይህ ሰው እግዚብሔር ለእርሱ ያለውን ነገር እንዴት እንደሚያጣው ዝም ብላችሁ አስቡት። ነገር ግን ከቻላችሁ እጅ ለእጅ ተያያዙ፥ ሁለት ወይም ሦስት ሰዎች፥ እናም እርስ በእርሳችሁ እንዲህ ተባባሉ፥ "ሌላ ሽንፈት አያስገልግም! ማሸነፍ እንችላለን! ለማሸነፍ የሚያስችል በቂ ኃይል አለ! ጌታ አስቀድሞ ሥራውን ሠርቶታል።" ጌታ እንዲረዳን አንዳችሁ ለአንዳችሁ ጸልዩ። መሸነፍ የለብንም። በቂ ጸጋ፥ ለድል የሚሆን በቂ ኃይል አለ።

ኢየሱስ ሆይ፥ እናመሰግንሀለን።

በመንፈስ ቅዱስ አብሮን ለሠራ ለአምላካችን ለእስራኤል ቅዱስ የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ምስጋና ይሁን፥ አሜን።

ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ ትርጉም ሙሉነህ አዲሱ
Translated to Amharic by Muluneh Addisu Abdissa, matoughen@gmail.com